# የገንዘብ ሚኒስቴር

## ለልማት ፕሮጀክቶች እንዲውሉ ከቀረጥ ነፃ ወደ አገር የሚገቡ ተሽከርካሪዎችን ዓይነትና ብዛት ለመወሰን  የወጣ መመሪያ
## ቁጥር 942/2015

**የገንዘብ ሚኒስቴር**
**ጥር 2015 ዓ.ም**

መመሪያ ቁጥር ____/2015

# ለልማት ፕሮጀክቶች እንዲውሉ ከቀረጥ ነፃ የተደረጉ ተሽከርካሪዎችን ዓይነትና ብዛት ለመወሰን የወጣ መመሪያ

የገንዘብ ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 129 እና በኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 517/2014 አንቀጽ 13 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "ለልማት ፕሮጀክቶች ከቀረጥ ነፃ ወደ አገር የሚገቡ ተሽከርካሪዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር ____/2015 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ:

1/ "ተሽከርካሪ" ማለት የደረቅ፣ የፍሳሽ ወይም የዝቃጭ ማስወገጃ ወይም ማቀዝቀዣ የተገጠመለት የጭነት መኪናን ወይም ለተለየ አገልግሎት ተብለው የሚዘጋጁ ተመሳሳይ ተሽከርካሪዎችን፤ አውቶቡስን፣ ሚኒባስን፤ ፤ሚዲባስን፤ ሸፍን የዕቃ ማጓጓዣ ተሽከርካሪን (ዴሊቨሪ ቫንን) እና ሞተር ብስክሌትን ይጨምራል፡፡

2/ "አውቶቡስ" ማለት ታጣፊ ወንበሮችን ሳይጨምር ቢያንስ 30 መቀመጫ ያለው የሰው ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ነው፡፡

3/ "ሚኒባስ" ማለት ታጣፊ ወንበሮችን ሳይጨምር ከ10 ያላነሰ እና ከ16 ያልበለጠ መቀመጫ ያለው የሰው ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ነው፡፡

4/ "ሚዲባስ" ማለት ታጣፊ ወንበሮችን ሳይጨምር ከ16 ያላነሰ እና ከ29 ያልበለጠ መቀመጫ ያለው የሰው ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ነው፡፡

5/ "ዴሊቨሪ ቫን" ማለት የመጫን አቅሙ ከ2500 ኪሎ ግራም ( ከሁለት ሺህ አምስት መቶ ኪሎ ግራም) በላይ የሆነ የጭነት ተሽከርካሪ ነው፡፡



የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት

6/ "የጭነት መኪና" ማለት ተሳቢውን ጨምሮ የመጫን አቅሙ ከ3500 ኪሎ ግራም( ከሶስት ሺህ አምስት መቶ ኪሎ ግራም) በላይ የሆነ ተሽከርካሪ ሲሆን ገልባጭ የጭነት መኪናን ይጨምራል።

7/ "ለተለየ አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ" ማለት ልዩ ባህርይ ላላቸው የሥራ መስኮች የሚውል በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 የተመለከተው አይነት ተሽከርካሪ ሲሆን፤ ለመደበኛ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎችን አይጨምርም።

8/ "ሞተር ብስክሌት" ማለት የሞተር አቅሙ ግምት ውስጥ ሳይገባ ባለሁለት ጎማ ተሽከርካሪ ነው።

9/ "ቀረጥ" ማለት ወደ አገር በሚገቡ ወይም በአገር ውስጥ በሚመረቱ ተሽከርካሪዎች ላይ የሚከፈል ማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነው።

10/ "ሆቴል" ማለት የመኝታ፣ የምግብ፤ የመጠጥ እና እንደአስፈላጊነቱም የመዝናኛ፤ የስብሰባና መሰል አገልግሎቶችን ለቱሪስቶችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያቀርብ ድርጅት ነው፤

11/ "ሎጅ" ማለት የመኝታ፤ የምግብና የመጠጥ አገልግሎቶችን እንደአስፈላጊነቱም የመዝናኛ፤ የስብሰባ እና መሰል አገልግሎቶችን በተፈጥሮ አካባቢዎች ለቱሪስቶችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያቀርብ ድርጅት ነው፤

12/ "ሬስቶራንት" ማለት የምግብና የመጠጥ አገልግሎት ለቱሪስቶችና ሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያቀርብ ድርጅት ነው፣

12/ "ሞቴል" ማለት የመኝታ፤ የመኪና ማቆሚያና እንደአስፈላጊነቱም የምግብ እና የመጠጥ አገልግሎቶችን በከተማ፤ ከከተማ ውጪና በአውራ ጎዳና ላይ ለቱሪስቶችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች የሚያቀርብ ድርጅት ነው

14/ "ሪዞርት ሆቴል" ማለት ለመዝናናት ወይም የዕረፍት ጊዜን ለማሳለፍ በሚያስችል መልኩ ከከተማ ወጣ ብሎ በመዝናኛ ሥፍራዎች የሚቋቋም ዘመናዊ ሆቴል ነው።

15/ "የኢንዱስትሪ ፓርክ" በኢንዱስትሪ ፓርኮች አዋጅ ቁጥር 886/2007 የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል።

የገንዘብ የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2

16/ "የማዕድን ስራ" ማለት በማናቸውም አይነት ዘዴ ማዕድንን በገጸምድር ወይም በውሃ አካላት ከሚገኝ የማዕድን ክምችት ወይም ተራፊ የማዕድን ክምችት ውስጥ ለማውጣት የሚደረግ ስራ ሲሆን፣ ከዚህ ጋር የተያያዘ ማከማቸትን፣ ማዘጋጀትን ፕሮሰስ ማድረግን (ማቅለጥን፣ ማጣራትን ሳይጨምር) ማጓጓዝንና መሸጥን እንዲሁም የጂኦተርማል ስራዎችን ይጨምራል።

17/ "ባለፈቃድ" ማለት በማዕድን እና በጂኦተርማል ሃብት ልማት አዋጅ መሰረት አግባብ ካለው ፈቃድ ሰጪ ባለስልጣን ማዕድናትን እና ጂኦተርማልን ለመመርመር ወይም ለማምረት የሚያስችል ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው።

18/ "የመንግስት መስሪያ ቤት" ማለት መሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በጀት የሚተዳደር በፌዴራል ወይም በክልል መንግስት በሚወጣ ሕግ የተቋቋመ መስሪያ ቤት ነው።

19/ "የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅት" በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011" የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል።

20/ "አዋጅ" ማለት የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 1180/2012 ነው።

21/ "ደንብ" ማለት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 517/2014 ነው።

22/ ከቀረጥ ነጻ ወደ አገር ማስገባት የሚለው ሀረግ በአገር ውስጥ የተመረተ ተሽከርካሪን ከቀረጥ እና ታክስ ሆኖ የመግዛት መብትን ይጨምራል።

23/ በኢንቨስትመንት አዋጅ እና በደንቡ እንዲሁም በማዕድን አዋጅ ለተለያዩ ቃላትና ሐረጎች የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 517/2014 አንቀጽ 13፣ በማዕድን ስራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 (እንደተሻሻለ)፣ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 (እንደተሻሻለ)፣ እንዲሁም የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ደንብን ለማሻሻል በወጣው ደንብ ቀጥር 89/1995 መሰረት ከፒካፕ እና ስቴሽን ዋገን በስተቀር ለልማት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያነት ወደአገር በሚገቡ ማንኛዉም ተሽከርካሪዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

የገንዘብ የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2

## ክፍል ሁለት

## ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገቡ የሚፈቀድላቸው የኢንቨስትመንት መስኮችና የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች ዓይነትና ብዛት

### 4. የማበረታቻው ተጠቃሚ የኢንቨስትመንት መስኮች

በኢንቨስትመንት ከተሰማሩ ባለሃብቶች መካከል ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥ ነፃ የማስገባት ማበረታቻ የሚሰጠው በማምረቻ ኢንዱስትሪ፣ የኢንዱስትሪ ፓርክ በማልማት፣ በግብርና፣ በሎጂስቲክስ፣ በኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት፣ ከኮከብ ደረጃ ባላቸው ሆቴሎች (የሪዞርት ሆቴሎችን ጨምሮ)፣ በባቡር መሠረተ ልማት፣ ሞቴሎች፣ ሬስቶራንቶችና ሎጆች፣ በመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ልማት፣ በአስጎብኝነት ሥራ እና በኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ ማስተላለፊያና ማሠራጫ፣ በትምህርትና ስልጠና፣ የጤና አገልግሎት፣ የአርኪቴክቸር እና ኢንጅነሪንግ ስራዎች የቴክኒክ ምርመራና ትንተና አገልግሎት እና ንግድ የሥራ መስኮች አዳዲስ ፕሮጀክቶችን ለሚያቋቁሙ ወይም ነባር ድርጅታቸውን ለሚያስፋፉ ባለሀብቶች ብቻ ይሆናል።

### 5. ለማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

1/ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ አንድ ከተመለከቱት የሥራ መስኮች በአንዱ የተሰማራ ማንኛውም ባለሀብት የኢንቨስትመንት ሥራውን የሚያከናውንበትን አካባቢ እና የተሠማራበትን የሥራ መስክ መሠረት በማድረግ በሠንጠረዥ አንድ የተመለከተውን ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀዳል።

2/ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ አንድ ከተዘረዘሩት የማምረቻ ኢንዱስትሪ የኢንቨስትመንት መስኮች መካከል በአንዱ የሚሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ የሚፈቀደው ባለሀብቱ፡-

ሀ) መሬት ስለማግኘቱ (የፋብሪካ ሕንፃ ወይም የመስሪያ ቦታ ተከራይቶም ከሆነ ሕጋዊ የኪራይ ውል) ማስረጃ፣

ለ) የፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ ማለትም የመሬት ዝግጅት፣ መሠረተ-ልማት፣ መጋዘን፣ መንገድ እና የመሳሰሉት ሥራዎች እየተከናወኑ ስለመሆናቸው ፕሮጀክቱ ካለበት የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት የተሰጠውን ማስረጃ፣

የገቢዎች ... የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት

ሐ) ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ የካፒታል ዕቃዎች ከውጭ አገር ስለመግዛታቸው ቢል ኦፍ ሎዲንግ ወይም ኤርዌይ ቢል ወይም ትራክዌይ ቢል እና የግዢ ደረሰኝ ወይም የካፒታል ዕቃዎቹ ከሀገር ውስጥ የተገዙ ከሆነ የግዢውን ውል ከአስፈላጊ ማስረጃዎች ጋር፣

መ) ባለሀብቱ የፋብሪካ ሕንፃ ተከራይቶ የሚሠራ ከሆነ የመሣሪያ ተከላ ስለመጀመሩ ፕሮጀክቱ ካለበት የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት የተሰጠውን ማስረጃ፣ እና

ሠ) በባንክ ብድር የሚገዛ ከሆነ የብድሩ ስምምነት ሰነድ እና/ወይም በራስ ገንዘብ የሚገዛ ከሆነ የቀረጥ ነጻ ማመልከቻ ከመቅረቡ በፊት ባሉት ሶስት ወራት በባንክ ሂሳቡ ያለውን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ ወቅታዊ የባንክ መግለጫ፣ ወይም የቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ነው።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ከፊደል ተራ "ሀ" እስከ "ሠ" የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ባለሀብት ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀድለት የኢንቨስትመንት ትግበራውን አጠናቅቆ የሙከራ ምርት ማምረት ስለመጀመሩ አግባብ ካለው አካል የተሰጠውን ማስረጃ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ይሆናል።

## 6. ለግብርና ኢንቨስትመንት የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

1/ ለግብርና ልማት ኢንቨስትመንት ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው ወደ አገር እንዲገቡ የሚፈቀደው ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ሁለት መሠረት ነው:

2/ በሠንጠረዥ ሁለት ከተመለከቱት የግብርና ልማት የኢንቨስትመንት መስኮች ቢያንስ በአንዱ የሚሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ከቀረጥ ነፃ የሚያስገባው ተሽከርካሪ አይነት እና ብዛት የሚወሰነው በሚያለማው የመሬት ሥፋት፣ በሚኖረው የእንስሣት ብዛት፣ የቀፎ ብዛት፣ የሰው ሠራሽ ኩሬ ይዘት ወይም ለፕሮጀክቱ ባዋለው የመሬት ሥፋት መሰረት ነው።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሀብቱ ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀድለት፣



የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት

ሀ) መሬት ስለማግኘቱ ወይም ተከራይቶም ከሆነ የኪራይ ውል ማስረጃ፣

ለ) የፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ ማለትም የመሬት ዝግጅት፣ መሠረተ ልማት፣ መጋዘን፣ መንገድ እና የመሣሠሉት ሥራዎች እየተከናወኑ ስለመሆናቸው ፕሮጀክቱ ከሚገኝበት ክልል የኢንቨስትመንት መ/ቤት የተሰጠውን ማስረጃ፣ እና

ሐ) ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ የካፒታል ዕቃዎች ከውጭ ሀገር ስለመግዛታቸው ቢል ኦፍ ሌዲንግ ወይም ኤርዌይ ቢል ወይም ትራክዌይ ቢል እና የግዢ ደረሰኝ፣ ወይም የካፒታል ዕቃዎቹ ከሀገር ውስጥ የተገዙ ከሆነ የግዢውን ውል ከአስፈላጊ ማስረጃዎች ጋር፣እና

መ) በባንክ ብድር የሚገዛ ከሆነ የብድሩ ስምምነት ሰነድ እና/ወይም በራስ ገንዘብ የሚገዛ ከሆነ የቀረጥ ነጻ ማመልከቻ ከመቅረቡ በፊት ባሉት ሶስት ወራት በባንክ ሂሳቡ ያለውን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ ወቅታዊ የባንክ መግለጫ፣ ወይም

የቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከፊደል ተራ 'ሀ' እስከ 'መ' የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም ባለሀብት ከሞተር ብስክሌት በስተቀር ሌሎቹን ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀድለት የኢንቨስትመንት ትግበራውን አጠናቅቆ የሙከራ ምርት ማምረት ስለመጀመሩ አግባብ ካለው አካል የተሰጠውን ማስረጃ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ይሆናል፡፡

5/ ባለሀብቱ የኢንቨስትመንት ትግበራውን አጠናቅቆ የማምረት ሥራ ሲጀምር ያለማው የመሬት ስፋት ወይም ያለው የእንስሳት ብዛት ወይም የቀፎ ብዛት ወይም የሰው ሠራሽ ኩሬ ይዘት ወይም ለፕሮጀክቱ ያዋለው የመሬት ሥፋት ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ ሁለት የተመለከተውን መጠን የሚያሟላ መሆኑን የሚያረጋግጥ የንግድ ሥራ ፈቃድ ካወጣበት አካል የተሰጠውን ማስረጃ የቀረጥ ነፃ መብቱን ለፈቀደው አካል ማምረት ከጀመረበት ቀን አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ማቅረብ ያለበት ሲሆን፣ ማስረጃውን ካላቀረበ ወይም መጠኑ ከተመለከተው በታች ሆኖ ከተገኘ ከቀረጥ ነፃ ባስገባው/ቸው ተሽከርካሪ/ዎች ላይ ተገቢውን ቀረጥ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

## 7. ለኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭ ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

1/ በኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት የተሠማራ እና የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሠጠው ማንኛውም ባለሀብት ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀድለት ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ሶስት በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

2/ በኮንስትራክሽን ስራ የተሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆኖ ወደአገር እንዲያስገባ የሚፈቀድለት ባለሀብቱ፡-

ሀ) ለስራው የሚያስፈልጉ ተሽከርካሪዎች ከውጭ ሀገር ስለመገዛታቸው ቢ.ል ኦፍ ሎዲንግ ወይም ኤርዌይ ቢ.ል ወይም ትራክዌይ ቢ.ል እና የግዢ ደረሰኝ ፣ ወይም

ለ) ተሽከርካሪዎቹን ከአገር ውስጥ የገዛ ከሆነ የግዢ ውሉን ከአስፈላጊ ሠነዶች

ሐ) በባንክ ብድር የሚገዛ ከሆነ የብድሩ ስምምነት ሰነድ እና/ወይም በራስ ገንዘብ የሚገዛ ከሆነ የቀረጥ ነጻ ማመልከቻ ከመቅረቡ በፊት ባሉት ሶስት ወራት በባንክ ሂሳቡ ያለውን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ ወቅታዊ የባንክ መግለጫ፣

የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

## 8. የኮከብ ደረጃ ላላቸው የሆቴል (ሪዞርት ሆቴልን ጨምሮ)፣ የሞቴል፣ የሬስቶራንትና የሎጅ አገልግሎት ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

1/ የኮከብ ደረጃ ባለው የሆቴል (ሪዞርት ሆቴልን ጨምሮ)፣ የሞቴል፣ የሬስቶራንት ወይም የሎጅ አገልግሎት የተሠማራ እና የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሠጠው ማንኛውም ባለሀብት የቱሪዝም ሚኒስቴር የሚያወጣውን የደረጃ መሥፈርት ማሟላቱ ሲረጋገጥና ማስረጃ ሲያቀርብ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ አራት መሰረት ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥ ነጻ ሆኖ ማስገባት ይችላል፡፡

2/ የኮከብ ደረጃ ባለው የሆቴል (ሪዞርት ሆቴልን ጨምሮ) ፣የሞቴል፣ የሬስቶራንት ወይም የሎጅ አገልግሎት የሚሠማራ ማንኛውም ባለሀብት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ተሽከርካሪ ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ ሆኖ ሊያስገባ የሚችለው የግንባታ ስራውን ያጠናቀቀ መሆኑ አግባብ ባለው አካል ሲረጋገጥ ወይም ሕንፃው በኪራይ ውል የሚገኝ ከሆነ የኪራይ ውሉ ሲቀርብ ነው፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ከተመለከተው በተጨማሪ የኮከብ ደረጃ ባለው የሆቴል (ሪዞርት ሆቴልን ጨምሮ)፣ የሞቴል፣ የሬስቶራንት ወይም የሎጅ አገልግሎት የሚሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆኖ ወደ አገር እንዲያስገባ የሚፈቀድለት ባለሀብቱ፦

ሀ) ለስራው የሚያስፈልጉ ተሽከርካሪዎች ከውጭ ሀገር ስለመግዛታቸው ቢል ኦፍ ሎዲንግ ወይም ኤርዌይ ቢል ወይም ትራክዌይ ቢል እና የግዢ ደረሰኝ ፣ ወይም

ለ) ተሽከርካሪዎቹን ከአገር ውስጥ የገዛ ከሆነ የግዢ ውሉን ከአስፈላጊ ሠነዶች፣

ሐ) በባንክ ብድር የሚገዛ ከሆነ የብድሩ ስምምነት ሰነድ እና/ወይም በራስ ገንዘብ የሚገዛ ከሆነ የቀረጥ ነጻ ማመልከቻ ከመቅረቡ በፊት ባሉት ሶስት ወራት በባንክ ሂሳቡ ያለውን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ ወቅታዊ የባንክ መግለጫ፣

የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

9. <u>ለመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ልማት ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች</u>

1/ ማንኛውም በመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ልማት ኢንቨስትመንት መስክ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሠጠው ባለሀብት ሶስት ዶል.ቨሪ ቫን ከቀረጥ ነጻ ሆኖ ወደ አገር እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡

2/ በመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ኢንቨስትመንት የተሰማራ ባለሃብት ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆኖ ወደአገር እንዲያስገባ የሚፈቀድለት ባለሀብቱ፦

ሀ) ለስራው የሚያስፈልጉ ተሽከርካሪዎች ከውጭ ሀገር ስለመግዛታቸው ቢል ኦፍ ሎዲንግ ወይም ኤርዌይ ቢል ወይም ትራክዌይ ቢል እና የግዢ ደረሰኝ ፣ ወይም

ለ) ተሽከርካሪዎችን ከአገር ውስጥ የገዛ ከሆነ የግዢ ውሉን ከአስፈላጊ ሠነዶች፣

የገንዘብ
የሪከርድ
አስተዳደር

ሐ) በባንክ ብድር የሚገዛ ከሆነ የብድሩ ስምምነት ሰነድ እና/ወይም በራስ ገንዘብ የሚገዛ ከሆነ የቀረጥ ነጻ ማመልከቻ ከመቅረቡ በፊት ባሉት ሶስት ወራት በባንክ ሂሳቡ ያለውን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ ወቅታዊ የባንክ መግለጫ፣

የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

10. **ለአስጎብኝነት አገልግሎት ኢንቨስትመንቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች**

1/ በአስጎብኝነት የሥራ መስክ የተሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ሁለት ሚኒባስ፤ ሁለት ሚዲባስ እና ሁለት አውቶቡስ ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡

2/ በአስጎብኝነት ኢንቨስትመንት መስክ የተሠማራ ማንኛውም ባለሀብት በዚህ አንቀጽ መሰረት ወደአገር ያስገባውን ተሽከርካሪ ማከራየት ወይም ከአስጎብኚነት ስራ ውጪ ማዋል አይችልም፡፡

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት ተሽከርካሪዎቹን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀደው ባለሀብቱ፡

ሀ) የቱሪዝም ሚኒስቴር ያወጣውን መሥፈርት በማሟላት አግባብ ካለው አካል የማስጎብኘት አገልግሎት ፈቃድ አውጥቶ/አግኝቶ ወደ ኢንቨስትመንት መስኩ የሚሠማራ ከሆነ፤

ለ) ተሽከርካሪዎቹ አዳዲስ ስለመሆናቸው ከተፈበረኩበት/ባቸው ፋብሪካ/ዎች ወይም ከአቅራቢዎች ማስረጃ ሲያቀርብ እና ተሽከርካሪዎቹን ለማስጎብኘት ሥራ ብቻ እንደሚያውላቸው በጉምሩክ ኮሚሽን ፊት ቀርቦ ግዴታ ሲገባ፤

ሐ) ለስራው የሚያስፈልጉ ተሽከርካሪዎች ከውጭ ሀገር ስለመገዛታቸው ቢል ኦፍ ሎዲንግ ወይም ኤርዌይ ቢል ወይም ትራክዌይ ቢል እና የግዢ ደረሰኝ ፣ ወይም

መ) ተሽከርካሪዎቹን ከአገር ውስጥ የገዛ ከሆነ የግዢ ውሉን ከአስፈላጊ ሠነዶች፣ እና

ሠ) በባንክ ብድር የሚገዛ ከሆነ የብድሩ ስምምነት ሰነድ እና/ወይም በራስ ገንዘብ የሚገዛ ከሆነ የቀረጥ ነጻ ማመልከቻ ከመቅረቡ በፊት ባሉት ሶስት ወራት በባንክ ሂሳቡ ያለውን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ ወቅታዊ የባንክ መግለጫ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

4/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) መሠረት ለአስጎብኝነት ሥራ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው የሚገቡ ተሽከርካሪዎችን ለመለየት በቱሪዝም ሚኒስቴር በሚወሰነው መሠረት የመለያ ምልክት እንዲኖራቸው ይደረጋል::

11. <u>ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ ማስተላለፊያና ማሠራጫ ኢንቨስትመንቶች እንዲውሉ ከቀረጥ ነጻ የሚገቡ ተሽከርካሪዎች</u>

1/ በኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ ማስተላለፊያና ማሠራጫ የኢንቨስትመንት መስክ የሚሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ አምስት በተመለከተው መሰረት ተሽከርካሪዎችን ከውጭ አገር ከቀረጥ ነፃ ማስገባት ይችላል:::

2/ በኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ ማስተላለፊያና ማሠራጫ የኢንቨስትመንት መስክ የሚሠማራ ማንኛውም ባለሀብት በዚህ አንቀጽ መሰረት ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥ ነጻ ሊያስገባ የሚችለው፣

ሀ) ተሽከርካሪዎቹ ከውጭ ሀገር ስለመግዛታቸው ቢል አፍ ሎዲንግ ወይም ኤርዌይ ቢል ወይም ትራክዌይ ቢል እና የግዢ ደረሰኝ ፣ ወይም

ለ) ሽከርካሪዎቹን ከአገር ውስጥ የገዛ ከሆነ የግዢ ውሉን ከአስፈላጊ ሠነዶች፣

ሐ) በባንክ ብድር የሚገዛ ከሆነ የብድሩ ስምምነት ሰነድ እና/ወይም በራስ ገንዘብ የሚገዛ ከሆነ የቀረጥ ነጻ ማመልከቻ ከመቅረቡ በፊት ባሉት ሶስት ወራት በባንክ ሂሳቡ ያለውን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ ወቅታዊ የባንክ መግለጫ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ነው::

12. <u>ለሎጂስቲክስ ዘርፍ እንዲውሉ ከቀረጥ ነጻ የሚገቡ ተሽከርካሪዎች</u>

1/ በሎጂስቲክስ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ላይ የሚሰማራ ማንኛውም ባለሀብት ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ስድስት በተመለከተው መሰረት ተሽከርካሪዎችን በሚያስፈልገው መጠን ከውጭ አገር ከቀረጥ ነፃ ማስገባት ይችላል::

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀደው ባለሀብቱ፡

ሀ) አግባብ ካለው አካል የሎጂስቲክስ ኢንቨስትመንት ፈቃድ አውጥቶ በኢንቨስትመንት መስኩ የሚሠማራ ከሆነ፤

ለ) ተሽከርካሪዎቹ ከውጭ ሀገር ስለመግዛታቸው ቢል ኦፍ ሎዲንግ ወይም ኤርዌይ ቢል ወይም ትራክዌይ ቢል እና የግዢ ደረሰኝ ፤ ወይም

ሐ) ተሽከርካሪዎችን ከአገር ውስጥ የገዛ ከሆነ የግዢ ውሉን ከአስፈላጊ ሠነዶች፣

መ) በባንክ ብድር የሚገዛ ከሆነ የብድሩ ስምምነት ሰነድ እና/ወይም በራስ ገንዘብ የሚገዛ ከሆነ የቀረጥ ነጻ ማመልከቻ ከመቅረቡ በፊት ባሉት ሶስት ወራት በባንክ ሂሳቡ ያለውን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ ወቅታዊ የባንክ መግለጫ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

## 13. <u>የትምህርትና ስልጠና፣ የጤና አገልግሎት፣ የአርክቴክቸር እና ኢንጅነሪንግ ስራዎች የቴክኒክ ምርመራና ትንተና አገልግሎት እና ንግድ ኢንቨስትመንቶች ከቀረጥ ነጻ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች</u>

1/ በትምህርትና ስልጠና፣ የጤና አገልግሎት፣ የአርክቴክቸር እና ኢንጅነሪንግ ስራዎች የቴክኒክ ምርመራና ትንተና አገልግሎት እና ንግድ ኢንቨስትመንቶች መስክ የሚሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ሰባት በተመለከተው መሰረት ተሽከርካሪዎችን ከውጭ አገር ከቀረጥ ነፃ ማስገባት ይችላል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 በተመለከቱት የኢንቨስትመንት መስኮች የሚሠማራ ማንኛውም ባለሀብት በዚህ አንቀጽ መሰረት ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥ ነጻ ሊያስገባ የሚችለው፤

ሀ) አግባብ ካለው አካል በትምህርትና ስልጠና፣ የጤና አገልግሎት፣ የአርክቴክቸር እና ኢንጅነሪንግ ስራዎች የቴክኒክ ምርመራና ትንተና አገልግሎት እና ንግድ ኢንቨስትመንቶች ፈቃድ አውጥቶ በኢንቨስትመንት መስኩ የሚሰማራ ከሆነ፣

ለ) ተሽከረካሪዎቹ ከውጭ ሀገር ስለመግዛታቸው ቢል ኦፍ ሎዲንግ ወይም ኤርዌይ ቢል ወይም ትራክዌይ ቢል እና የግዢ ደረሰኝ፣ ወይም

ሐ) ተሽከርካሪዎቹን ከአገር ውስጥ የገዛ ከሆነ የግዢ ውሉን ከአስፈላጊ ሠነዶች ጋር፣ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

መ) በባንክ ብድር የሚገዛ ከሆነ የብድሩ ስምምነት ሰነድ እና/ወይም በራስ ገንዘብ የሚገዛ ከሆነ የቀረጥ ነጻ ማመልከቻ ከመቅረቡ በፊት ባሉት ሶስት ወራት በባንክ ሂሳቡ ያለውን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ ወቅታዊ የባንክ መግለጫ የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ መብቱን ለሚፈቅደው አካል ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

## 14. <u>የሠራተኛ ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች</u>

1/ በአስጎብኝነት ኢንቨስትመንት ሥራ መስኮች ላይ የሚሠማሩትን ሳይጨምር በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 በተመለከቱት የኢንቨስትመንት መስኮች የተሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ለሠራተኛ ማጓጓዣ የሚያስፈልገውን ተሽከርካሪ እንደ ፕሮጀክቱ የሠራተኛ ብዛት ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ስምንት በተመለከተው መሠረት ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሠራተኛ ማጓጓዣ ተሽከርካሪን ከቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀደው ባለሀብቱ በቅድሚያ፣

ሀ) መሬት ስለማግኘቱ/ተከራይቶም ከሆነ የኪራይ ውል ማስረጃ፣

ለ) ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ ተሽከርካሪዎች ከውጭ አገር ተገዝተው ስለመጫናቸው ቢል ኦፍ ሌዲንግ ወይም ኤርዌይ ቢል ወይም ትራክዌይ ቢል እና የግዢ ደረሰኝ፣ ወይም

ሐ) ተሽከርካሪዎቹ ከአገር ውስጥ የተገዙ ከሆነ የግዢ ውል ከአስፈላጊ ሰነዶች ጋር፣

መ) ፕሮጀክቱ የማምረት ወይም አገልግሎት የመስጠት ስራ ስለመጀመሩ ፕሮጀክቱ ከሚገኝበት ኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት ማስረጃ፣ እና

ሠ) ለፕሮጀክቱ በቋሚነት ተቀጥረው በመሥራት ላይ የሚገኙ ሠራተኞችን ሥም ዝርዝር የያዘ ቢያንስ የሦስት ወር የደመወዝ መክፈያ ሰነድ (Pay-roll) እና ለመንግሥት የደመወዝ ግብር የተከፈለበት ማስረጃ፤

ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

የገንዘብ የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት

15. **ለተለየ አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ስለማስገባት**

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 እና 5 የተመለከተው ቢኖርም በሎጂስቲክስ አገልግሎት ወይም ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ አንድ እና ሁለት ከተመለከቱት የሥራ መስኮች በአንዱ የተሠማራ ባለሀብት እንደተሠማራበት ፕሮጀክት ባህሪ እየታየ ማቀዝቀዣ የተገጠመለት ተሽከርካሪ ወይም ለእንስሳት ማጓጓዣ የሚውል ልዩ ተሽከርካሪ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ከውጭ አገር እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡

2/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 የተመለከተው ቢኖርም ማናቸውም የማምረቻ ኢንዱስትሪ አንድ የፍሳሽ/የዝቃጭ ማስወገጃ ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነፃ ሆኖ ከውጭ አገር እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡

3/ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 4 በተመለከቱት የሥራ መስኮች የተሠማራ ማንኛውም ባለሀብት ለሠራተኞች የአደጋ ጊዜ አገልግሎት የሚውሉ አምቡላንሶችን ከቀረጥ ነፃ ሆኖ ከውጭ አገር እንዲያስገባ ይፈቀድለታል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የማዕድን ስራዎች

16. **ለማዕድን ስራዎች የሚውሉ ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥ ነጻ ስለማስገባት**

1/ ማንኛውም የምርመራ፣ የአነስተኛ ደረጃ፣ የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ስራ ወይም ምርመራ እና ማምረትን ያጣመረ ፈቃድ ያለው ሰው ወይም አግባብ ባለው ህግ መሰረት የተደራጀ የማዕድን የህብረት ስራ ማህበር ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ ዘጠኝ የተመለከቱትን ተሽከርካሪዎች ከቀረጥ ነጻ ለማስገባት ይችላል፡፡

2/ ማንኛውም የማዕድን ፍለጋ ባለፈቃድ ወይም የባህላዊ ማዕድን ማምረት ስራ ባለፈቃድ ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥ ነጻ ማስገባት አይፈቀድለትም፡፡

17. **ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥ ነፃ ማስገባት የሚፈቀድበት ሁኔታ**

ከቀረጥ ነፃ ሆነው ወደአገር የሚገቡ ተሽከርካሪዎች አይነት እና ብዛት በማዕድን ፈቃድ አይነት፣ በማዕድን አይነት እና በፕሮጀክቱ አጠቃላይ የኢንቨስትመንት መጠን ላይ ተመስርቶ የተወሰነ ሲሆን፣ ዝርዝሩ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ 9 የተመለከተው ነው፡፡

## 18. ማስረጃዎችን ስለማቅረብ

- በማዕድን ስራዎች የሚሰማራ ባለሀብት በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን ተሽከርካሪዎች ከቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚፈቀድለት የሚከተሉትን ማስረጃዎች ሲያቀርብ ይሆናል፣

1/ አግባብ ባለው ፈቃድ ሰጪ ባለስልጣን የተሰጠውን ከዋናው ቅጂ ጋር የተገናዘበ የማዕድን ስራ ፈቃድ፣ የህበረት ስራ ማህበር ከሆነ አግባብ ካለው ባለስልጣን የተሰጠውን የምስክር ወረቀት እና የማዕድን ስራ ፈቃድ፣

2/ የፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ ማለትም የካምፕ ዝግጅት፣ መሠረተ ልማት፣ እና የመሣሠሉት ሥራዎች እየተከናወኑ ስለመሆናቸው ከፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የተሰጠውን ማስረጃ፣

3/ የማዕድን ማምረት ስራ ሲሆን፣ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ የካፒታል ዕቃዎች ከውጭ ሀገር ስለመገዛታቸው የግዢ ደረሰኝ፣ ቢል ኦፍ ሌዲንግ ወይም ኤርዌይ ቢል ወይም ትራክዌይ ቢል እና የግዢ ደረሰኝ ወይም ተሽከርካሪዎችን ከአገር ውስጥ የገዛ ከሆነ የግዢ ውሉን ከአስፈላጊ ሠነዶች፣

4/ በባንክ ብድር የሚገዛ ከሆነ የብድሩ ስምምነት ሰነድ እና/ወይም በራስ ገንዘብ የሚገዛ ከሆነ የቀረጥ ነጻ ማመልከቻ ከመቅረቡ በፊት ባሉት ሶስት ወራት በባንክ ሂሳቡ ያለውን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ ወቅታዊ የባንክ መግለጫ፣ እና

5/ የሰራተኛ ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች ከቀረጥ ነጻ ለማስገባት ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ ለፕሮጀክቱ ተቀጥረው በመስራት ላይ የሚገኙ ሰራተኞችን የስም ዝርዝር የያዘ የደመወዝ መክፈያ ሰነድ እና ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ለታክስ ባለስልጣኑ ግብር የተከፈለበት ማስረጃ፡፡

የገንዘብ
የሪከርድ
አስተዳደር
አገልግሎት

## ክፍል አራት

## ለመንግስት መስሪያ ቤቶች እና ለሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች ዓይነትና ብዛት

### 19. የተሽከርካሪዎች አይነት እና ብዛት

የመንግስት መስሪያ ቤቶች እና የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች ለሚያከናውኑዋቸው ፕሮጀክቶች የሚያስፈልጉ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዙ ሠንጠረዦች የተመለከቱ የተሽከርካሪዎችን አይነት በፕሮጀክቱ በተመለከተው ብዛት ከቀረጥ ነፃ ማስገባት ወይም ከአገር ውስጥ መግዛት ይችላሉ፡፡

### 20. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው ሰነዶች

1/ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19 መሰረት ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥ ነጻ ማስገባት ወይም ከአገር ውስጥ መግዛት የሚችሉት የሚከተሉትን ሰነዶች ሲያቀርቡ ይሆናል፤

ሀ) ተሽከርካሪው አገልግሎት የሚሰጥበት ፕሮጀክት አግባብ ባለው የፌዴራል መንግስት ወይም የክልል መስተዳደር መስሪያ ቤት የጸደቀ መሆኑን የሚያረጋግጥ ከመንግስት መስሪያ ቤቱ ጋር የተፈረመ የስምምነት ሰነድ፤

ለ) ፕሮጀክቱ ሊጠናቀቅ ከስድስት ወር በላይ የቀረው መሆኑን የሚያስረዳ የፕሮጀክት ፕሮፖዛል፤

ሐ) ድርጅቱ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን የተመዘገበ መሆኑን የሚያሳይ የታደሰ የማህበራት ምዝገባ ሰርተፊኬት፤

መ) በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቱ ስም የተዘጋጀ የተሽከርካሪው ማስጫኛ ሰነድ፣ ወይም ኤርዌይ ቢል ወይም ትራክዌይ ቢል፣ የተገዛበት ደረሰኝ፣ የማሸጊያ ዝርዝር፤

ሠ) ተሽከርካሪው ከአገር ውስጥ የተገዛ ከሆነ የግዢ ውል ከአስፈላጊ ሰነዶች ጋር፤

ረ) ተሽከርካሪው በእርዳታ የተገኘ ከሆነ የእርዳታ የምስክር ወረቀት፤ እና

ሰ) በሚመለከተው ተቆጣጣሪ የመንግስት አካል የተጻፈ የድጋፍ ደብዳቤ፡፡

የገንዘብ የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2

2/ በዚህ መመሪያ መሰረት ከቀረጥ ነጻ የገባን ተሽከርካሪ ለሌላ ወገን ማስተላለፍ የሚቻለው በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011 አንቀጽ 46 እና ጸንተዉ በስራ ላይ ባሉ የጉምሩክ ሕጎች መሰረት ብቻ ነው፡፡

3/ ፕሮጀክቱ በመጠናቁ ወይም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቱ በመፍረሱ ምክንያት ሒሳብ አጣሪው ወይም የሲቪል ማህበረሰብ ባለሥልጣን ከቀረጥ ነጻ የገባው ተሽከርካሪ ለሌላ ድርጅት እንዲተላለፍ ከመወሰኑ በፊት ይህንኑ ለገንዘብ ሚኒስቴር ማስታወቅ አለበት፡፡

## 21. የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚያቀርቧቸው ሰነዶች

የመንግስት መስሪያ ቤቶች ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዙ ሰንጠረገች የተዘረዘሩ ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥ ነጻ ማስገባት ወይም ከአገር ውስጥ መግዛት የሚችሉት የሚከተሉትን ሰነዶች ሲያቀርቡ ይሆናል፤

1/ መስሪያ ቤቱ ተሽከርካሪው ከቀረጥ ነጻ እንዲሆን ጥያቄ ያቀረበበት ደብዳቤ፤

2/ ለፕሮጀክቱ የሚውለውን ተሽከርካሪ ለመግዛ እንዲውል የተፈደው በጀት፤

3/ የተሽከርካሪው ማስጫኛ ሰነድ፤ የተገዛበት ደረሰኝ፣ የማሸጊያ ዝርዝር ፤

4/ ተሽከርካሪው በእርዳታ የተገኘ ከሆነ በእርዳታ የተሰጠ መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት፣ እና

5/ በሚመለከተው አካል የፀደቀ የፕሮጀክት ሰነድ፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 22. በአገር ውስጥ ስለሚገጣጠሙ/ስለሚመረቱ ተሽከርካሪዎች

በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሰረት ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ የሚፈቀድለት ተጠቃሚ ከአገር ውስጥ የተሽከርካሪ መገጣጠሚያ/ማምረቻ ፋብሪካ ተሽከርካሪ ሲገዛ ተሽከርካሪውን ለማምረት ከውጭ ተገዝተው በገቡ እና ከአገር ውስጥ በተገዙ የተሽከርካሪው ግብዓቶች ላይ የተከፈለው ቀረጥ ተሠልቶ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

የገንዘብ የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት

## 23. የማስፋፊያ/የማሻሻያ ስራዎች

በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 4 እና 16 ከተዘረዘሩት የኢንቨስትመንት/የማዕድን ስራ መስኮች መካከል በአንዱ የተሠማራ ነባር ድርጅቱን ያስፋፋ/ያሻሻለ ባለሀብት ለማስፋፊያ/ለማሻሻያ ፕሮጀክቱ በአንቀጽ 3፣ 4፣ 9፣ 10 እና እንደ አግባብነቱ በአንቀጽ 11 እና 15 ከተመለከቱት እያንዳንዱ ተሽከርካሪ ዓይነት አንድ ተሽከርካሪ በነዚሁ አንቀጾች በተደነገገው መሠረት ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

## 24. ክልከላ

በዚህ መመሪያ ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነጻ እንዲያስገባ የተፈቀደለት ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት፡

1/ ከቀረጥ ነጻ ያስገባውን ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነጻ እንዲገባ ከተደረገበት አላማ ውጪ ሊያውል አይችልም፡፡

2/ ከቀረጥ ነጻ እንዲገባ ከተደረገበት አላማ ውጪ ሲጠቀምበት ከተገኘ በተሽከርካሪው ላይ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ መክፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በጉምሩክ ሕግ መሰረት አስፈላጊው ሕጋዊ እርምጃ ተፈጻሚ ይሆንበታል፡፡

## 25. የተሻሩ እና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች

1/ ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ስለሚፈቀድበት ሁኔታ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ የወጣው መመሪያ ቁጥር 4/2005 ተሽሯል፡፡

2/ ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ነጻ ለማስገባት ስለሚፈቀድበት ሁኔታ ለመደንገግ በማዕድን ሚኒስቴር የወጣው የማሻሻያ መመሪያ ቁጥር 4/2001 ተሽሯል፡፡

3/ መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ከጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ነጻ ስለሚያስገቧቸው ዕቃዎች የወጣው መመሪያ ቁጥር 79/2005 ውስጥ ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነፃ ማስገባትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፤

4/ ይህን መመሪያ የሚቃረን ማናቸውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ መመሪያ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

የገንዘብ የሪከርድ አስተዳደር

## 26. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1/ የዚህ መመሪያ አንቀጽ 25(1) እና (2) ድንጋጌ ቢኖርም ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወይም የማዕድን ፍለጋ እና የማልማት ፈቃድ የወሰዱ ድርጅቶችን በሚመለከት፣ ስቴሽን ዋገንን እና ፒካፕ ተሽከርካሪን ሳይጨምር፣ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ እንደገና ተሻሽሎ የወጣው መመሪያ ቁጥር 4/2005 እና በማዕድን ሚኒስቴር የወጣው መመሪያ ቁጥር 4/2001 ተፈጻሚነት ይቀጥላል::

2/ የዚህ መመሪያ አንቀጽ 25(3) ድንጋጌ ቢኖርም ይህ መመሪያ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ከጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ነጻ ስለሚያስገቧቸው እቃዎች በወጣው መመሪያ ቁጥር 79/1995 መሰረት ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥ ነጻ ለማስገባት የተፈቀደላቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት በመመሪያ ቁጥር 79/1995 የተፈቀደላቸውን ተሽከርካሪ ወደአገር ማስገባት ይችላሉ::

## 27. መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን

ይህ መመሪያ በገንዘብ ሚኒስቴር የድህረ ገጽ አድራሻ ከተለጠፈበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ________ ቀን 2015 ዓ.ም.

አህመድ ሺዴ
የገንዘብ ሚኒስትር

## ሠንጠረዥ አንድ

## ለማምረቻ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንቶች ከቀረጥ ነጻ ሆነው እንዲገቡ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች (በኢንቨስትመንት ሥራ መስኮችና በአስተዳደር አካባቢዎች)

| የኢንቨስትመንት ሥራ መስክ | የኢንቨስትመንት ቦታ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | | በሌሎች አካባቢዎች | |
| | ሽፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና | ሽፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና |
| 1. <u>የምግብ ኢንዱስትሪ</u> | | | | |
| 1.1. ሥጋና የሥጋ ውጤቶች ማቀነባበርና መጠበቅ | ሁለት | አንድ | ሶስት | ሁለት |
| 1.2. ዓሣና የዓሣ ውጤቶችን ማቀነባበር | ሁለት | አንድ | ሶስት | ሁለት |
| 1.3. አትክልትና ፍራፍሬ ማቀነባበርና መጠበቅ | ሁለት | አንድ | ሶስት | ሁለት |
| 1.4. የምግብ ዘይት ማምረት | አንድ | በሚያስፈልገው መጠን | አንድ | በሚያስፈልገው መጠን |
| 1.5. ወተት ማቀነባበር እና/ወይም የወተት ውጤቶችን ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 1.6. የምግብ ማሻሻያ፣ ተጨማሪዎች ወይም ንጥረ ነገሮች ወይም ስታርችና የስታርች ውጤቶችን ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 1.7. የእህል ምርት ውጤቶችን ማቀነባበር (የዱቄት ማምረትን ሳይጨምር) | አንድ | ሁለት | አንድ | ሁለት |
| 1.8. ስኳር ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 1.9. ማካሮኒ፣ ፓስታ እና/ወይም የመሳሰሉ ምግቦችን ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 1.10. አዮዲን የተጨመረበት ጨው ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ |
| 1.11. ሰው ሰራሽ ማር ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ |
| 1.12. ተቆልቶ የተፈጨ ቡና፣ የሚሟሟ ቡና፣ ሻይ ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ |
| 1.13. የእንስሳት መኖ ማቀነባበር | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ |

የገንዘብ የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2

| የኢንቨስትመንት ሥራ መስክ | የኢንቨስትመንት ቦታ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | | በሌሎች አካባቢዎች | |
| | ሽፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና | ሽፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና |
| 2. <u>የመጠጥ ኢንዱስትሪ</u> | | | | |
| 2.1. የአልኮል መጠጥ ማምረት | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 2.2. የወይን ጠጅ ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 2.3. ቢራ እና/ወይም የቢራ ብቅል ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 2.4. የማዕድን ወይም የታሸጉ ሌሎችውሃዎችን ማምረት | አንድ | ሁለት | ሁለት | ሦስት |
| 2.5. ለስላሳ መጠጥ ማምረት | አንድ | ሁለት | ሁለት | ሦስት |
| 3. <u>የጨርቃ ጨርቅና የስፌት ውጤቶች ኢንዱስትሪ</u> | | | | |
| 3.1. የተለያዩ የጨርቃ ጨርቅ ጭረቶችን ማዘጋጀት፣ መፍተል፣ መሸመን፣ ማጠናቀቅ እና/ወይም ማተም (አልባሳትን ሳይጨምር) | አንድ | አንድ | ሁለት | ሁለት |
| 3.2. ጣቃ ጨርቅ፣ ክር፣ ድርና ማግ፣ አልባሳትና ሌሎች የጨርቃ ጨርቅ ውጤቶችን በማንጣትን በማቅለም፣በማኮማተር፣በማፍካት፣በማጠንከር፣ወር ድንና ቁመትን በመጠበቅ ወይም በማስዋብ ማጠናቀቅ | አንድ | አንድ | ሁለት | ሁለት |
| 3.3. ከአልባሳት በስተቀር የተዘጋጁ ጨርቃ ጨርቆችን ወይም ሹራብ ፎጣ ወይም ምንጣፍ ማምረት | አንድ | አንድ | ሁለት | ሁለት |
| 3.4. የጨርቃ ጨርቅ አልባሳትን (የስፖርት አልባሳትን ጨምሮ) ወይም ተጓዳኝ አካላትን(አክሰሰሪስ) ማምረት | አንድ | አንድ | ሁለት | ሁለት |
| 4. <u>የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ</u> | | | | |
| 4.1. ቆዳና ሌጦ ማለስለስና ማጠናቀቅ (ካለቀለት ደረጃ በታች ቆዳና ሌጦ ማልፋትን አይጨምርም) | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 4.2. ካለቀለት ደረጃ በታች ቆዳና ሌጦ ማልፋት | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |

የገንዘብ
የሪከርድ
አስተዳደር
አገልግሎት

| የኢንቨስትመንት ሥራ መስክ | የኢንቨስትመንት ቦታ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | | በሌሎች አካባቢዎች | |
| | ሸፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና | ሸፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና |
| 4.3. የቆዳ ውጤቶች እና/ወይም ተጓዳኝ አካላትን(አክሰሰሪስ) ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 4.4. ቆዳ ወይም የቆዳ ምትክ ጫማ ማምረት | ሁለት | ሁለት | ሁለት | ሁለት |
| 5. የእንጨት ውጤቶች ኢንዱስትሪ | | | | |
| 5.1. የእንጨት ውጤቶችን (እንጨት መሰንጠቅን፣ ጣውላ ማምረትን እና ቀድመው የተዘጋጁ የእንጨት ውጤቶችን መገጣጠምን ሳይጨምር) ማምረት | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 6. የወረቀት እና የወረቀት ውጤቶች ኢንዱስትሪ | | | | |
| 6.1. ፐልፕ እና/ወይም ወረቀት ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 6.2. የወረቀት ውጤቶችን ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 7. የማተሚያ ኢንዱስትሪ | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 8. የኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶች ኢንዱስትሪ | | | | |
| 8.1. መሠረታዊ ኬሚካሎችን (ኢታኖልን እና/ወይም ሰው ሰራሽ ጭረቶችን ጨምሮ) እና/ወይም ሃይድሮጂን እና አሞኒያ ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 8.2. ማዳበሪያ እና/ወይም የናይትሮጅን ውህዶችን ማምረት | አይፈቀድም | በሚያስፈልገው መጠን | አይፈቀድም | በሚያስፈልገው መጠን |
| 8.3. መሰረታዊ (የመጀመሪያ ደረጃ) የፕላስቲክ እና/ወይም ሲንቴቲክ (የሰው ሠራሽ) ጎማ ጥሬ ዕቃዎችን እና ጎማ ውጤቶችን ማምረት | አይፈቀድም | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |
| 8.4 ፀረ-ተባይና የግብርና ኬሚካሎችን ማምረት | አንድ | ሁለት | አንድ | ሁለት |
| 8.5. ቀለም፣ ቫርኒሽ እና ተመሳሳይ ምርቶች፣ ማጣበቂያ እና/ወይም መሰረታዊ ያልሆኑ ኬሚካሎችን ማምረት | አንድ | ሁለት | አንድ | ሁለት |
| 8.6. የንፅህናና የኮስሞቲክስ ዕቃዎች እና ግብዓቶች መፈብረክ | አንድ | ሁለት | አንድ | ሁለት |

| የኢንቨስትመንት ሥራ መስክ | የኢንቨስትመንት ቦታ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | | በሌሎች አካባቢዎች | |
| | ሸፍን የጭነት መኪና (ዶሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና | ሸፍን የጭነት መኪና (ዶሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና |
| 9. <u>የመሠረታዊ መድኃኒት ምርት እና የመድኃኒት ኢንዱስትሪ</u> | | | | |
| 9.1. ለመድኃኒት ግብዓትነት የሚውሉ መሠረታዊ የመድኃኒት ውጤቶችን ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | ሁለት |
| 9.2. ለሰው አገልግሎት የሚውል መድኃኒት ማምረት(ክትባት ማምረትን ጨምሮ) | ሁለት | ሁለት | ሁለት | ሁለት |
| 9.3. ለእንስሳት አገልግሎት የሚውል መድኃኒት ማምረት(ክትባት ማምረትን ጨምሮ) | ሁለት | ሁለት | ሁለት | ሁለት |
| 9.4. ከመድኃኒት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን የማሸጊያ ምርቶች ማምረት | ሁለት | ሁለት | ሁለት | ሁለት |
| 9.5. የመድኃኒት ማሸግ ስራዎች | ሁለት | ሁለት | ሁለት | ሁለት |
| 10. <u>የፕላስቲክ ውጤቶች ኢንዱስትሪ</u> | | | | |
| 10.1. ፊስታልን ሳይጨምር የፕላስቲክ ውጤቶችን ማምረት | አይፈቀድም | አይፈቀድም | አይፈቀድም | አይፈቀድም |
| 11. <u>ብረት ያልሆኑ የማዕድን ውጤቶች ኢንዱስትሪ</u> | | | | |
| 11.1. መስታወት እና/ወይም የመስታወት ወይም የሴራሚክ ውጤቶችን ማምረት | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 11.2. ሲሚንቶ ማምረት | አይፈቀድም | በሚያስፈልገው መጠን | አይፈቀድም | በሚያስፈልገው መጠን |
| 11.3. የሸክላና የሲሚንቶ ውጤቶችን ማምረት | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| 11.4. የካባ ድንጋዮችን ማውጣትን ሳይጨምር የድንጋይ ውጤቶችን፣ ዕብነ በረድ እና ግራናይት የኖራ ድንጋይ መቁረጥ፣ ቅርፅ ማውጣት እና ማጠናቀቅ | አይፈቀድም | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |
| 11.5. ኖራ፣ ጀሶ እና/ወይም የመሳሰሉ መለሰኛዎችን ማምረት | አይፈቀድም | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |

የገንዘብ የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2

| የኢንቨስትመንት ሥራ መስክ | የኢንቨስትመንት ቦታ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | | በሌሎች አካባቢዎች | |
| | ሽፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና | ሽፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና |
| 12.<u>የመሠረታዊ ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ (የማዕድን ማውጣትን ሳይጨምር)</u> | | | | |
| 12.1. ብረት፣ የአረብ ብረት እና የብረት ማዕድናት ውጤቶችን መፈብረክ | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 12.2. መሠረታዊ የከበሩና የብረት ይዘት የሌላቸው ብረታ ብረቶችን ማምረት | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 12.3. ከብረት እና ማግኔታዊ ያልሆኑ ብረታ ብረቶች ማቅለጥ/ማድለብና የተለያዩ ቅርፆችን ማውጣት | አይፈቀድም | አንደ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 13. <u>ለስትራክቸር የሚያገለግሉ የብረታ ብረት ውጤቶች ኢንዱስትሪ</u> | | | | |
| 13.1. የማዋቀሪያ እና የተለያዩ ብረታ ብረት ውጤቶችን ማምረት (የቤት ክዳን ቆርቆሮ እና ሚስማርን ሳይጨምር) | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 14. <u>የኮምፒዩተር፣ የኤሌክትሮኒክስ እና የዕይታ ዕቃዎች ኢንዱስትሪ</u> | | | | |
| 14.1. ኮምፒዩተር እና ተጓዳኝ ዕቃዎችን እና/ወይም የኤሌክትሮኒክስ አካሎችንና ሰሌዳዎችን ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ |
| 14.2. የመገናኛ መሣሪያዎችን ወይም የፍጆታ ኤሌክትሮኒክስ (ቴሌቪዥን፣ ዲ.ቪ.ዲ፣ ሬድዮ እና የመሳሰሉት) ዕቃዎችን ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ |
| 14.3. የመለኪያ፣ የመፈተሻ፣ የመቃኛ፣ የመቆጣጠሪያ መሳሪያዎችን ወይም ሰዓት ማምረት | አንድ | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም |
| 14.4. የሕክምና መሣሪያዎችን ወይም እቅርቦቶችን ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ |
| 14.5. የሕክምና መሳሪዎችን መገጣጠም | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ |
| 14.6. የዕይታ ወይም የፎቶ ማንሻ ወይም መግነጢሳዊ እና የዕይታ ሚዲያ ዕቃዎችን ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ |

የገንዘብ
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት

| የኢንቨስትመንት ሥራ መስክ | የኢንቨስትመንት ቦታ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | | በሌሎች አካባቢዎች | |
| | ሸፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና | ሸፍን የጭነት መኪና (ዴሊቨሪቫን) | የጭነት መኪና |
| 15. <u>የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ኢንዱስትሪ</u> | | | | |
| 15.1. የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን ማምረት | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| 16 <u>የማምረቻ/አገልግሎት መስጫ መሣሪያዎችና ዕቃዎች ኢንዱስትሪ</u> | | | | |
| 16.1. ለሁለገብ አገልግሎት ሥራ የሚያገለግሉ መሣሪያዎችን ማምረት | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 16.2. ለልዩ አገልግሎት የሚውሉ መሣሪያዎችን ማምረት | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 17. <u>የመጓጓዣ ተሽከርካሪዎች እና ሌሎች የትራንስፖርት መሳሪያዎችን ማምረት</u> | | | | |
| 17.1. የሞተር ተሽከርካሪ(መኪና) ማምረት | አይፈቀድም | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |
| 17.2. የመኪና አካላትን፣ ተጎታችን እና/ወይም ከፊል ተጎታችን ወይም መለዋወጫዎችን እና ተጓዳኝ አካላትን ማምረት | አይፈቀድም | ሁለት | አይፈቀድም | ሁለት |
| 17.3. በባቡር እና በትራም መንገድ የሚሄዱ ሎኮሞቲቮችን እንዲሁም ዘዋሪ እግር ያላቸውን ተሽከርካሪዎች ጋሪዎችን ማምረት | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 17.4. የሞተር ብስክሌቶችን፣ ብስክሌቶችን እና ባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎችን መፈብረክ | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 17.5. ጀልባዎችን መገንባት | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 18. የቤትና የቢሮ ዕቃዎች (ከሴራሚክ የሚሠሩትን ሳይጨምር) ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ |
| 19. የእደጥበብ፣ የገፀበረከት ዕቃዎች፣ አርቲፊሻል ጌጣጌጥ፣ የሙዚቃ እና የስፖርት ዕቃዎችን ማምረት | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ |
| 20. ከግብርና ጋር የተቀናጀ የማምረት ኢንዱስትሪ | ሁለት | ሦስት | ሦስት | አራት |
| 21.የኢንዱስትሪ ፓርክ፣ የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ፓርክን ጨምሮ፣ ማልማት እና የማከራየት ስራዎች | ሁለት | ሦስት | ሦስት | አራት |

የገንዘብ * የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት * 2

## ሠንጠረዥ ሁለት

## ለግብርና ኢንቨስትመንቶች ከቀረጥ ነፃ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች
**(በኢንቨስትመንት ሥራ መስክና በአስተዳደር አካባቢዎች)**

| ግብርና | የሚለማው መሬት ስፋት (በሄክታር) | በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | | በሌሎች አካባቢዎች | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ሞተር ብስክሌት | የጭነት መኪና | ሞተር ብስክሌት | የጭነት መኪና |
| 1. የእርሻ ልማት | | | | | |
| 1.1. የዓመታዊ ሰብሎች ልማት | | | | | |
| 1.1.1.የብርዕና የአገዳ ሰብሎች ወይም የሸንኮራ ማልማት | 200-300 | አንድ | ሶስት | አንድ | ሶስት |
| | ከ300 በላይ -1000 | ሁለት | አራት | ሁለት | አራት |
| 1.1.2. የቅባት እህሎች ማልማት | ከ1000 በላይ-2000 | ሁለት | አምስት | ሶስት | አምስት |
| 1.1.3. የጥራጥሬ እህሎች ማልማት | ከ2000 በላይ-3000 | ሁለት | ስድስት | አራት | ስድስት |
| | ከ3000 በላይ-4000 | ሁለት | ሰባት | አምስት | ሰባት |
| | ከ5000 በላይ | ሶስት | ስምንት | ስድስት | ስምንት |
| 1.1.4 አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ እፅዋት እንዲሁም የተረጋገጠ ምርጥ ዘር ማምረት | ከ50-100 | አይፈቀድም | ሁለት | አንድ | ሁለት |
| | ከ100 በላይ | አይፈቀድም | አራት | አንድ | አራት |
| 1.1.5 የጭረት ሰብሎችን ማምረትና ማዘጋጀት | ከ50 በላይ | አንድ | አንድ | አንድ | አንድ |
| 1.1.6 የእንስሳት መኖ ማልማት፣ ለመድኃኒትነት፣ ለሽቶ፣ ለቅመምነት እና ለመሳሰሉት የሚሆኑ ሰብሎችን ማምረት | ከ10-30 | አይፈቀድም | አይፈቀድም | አይፈቀድም | አይፈቀድም |
| | ከ30 በላይ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | ሁለት |

| ግብርና | የሚለማው መሬት ስፋት (በሄክታር) | በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | | በሌሎች አካባቢዎች | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ሞተር ብስክሌት | የጭነት መኪና | ሞተር ብስክሌት | የጭነት መኪና |
| 1.2 <u>የመካከለኛ ጊዜ ቋሚ ተክሎች ማልማት</u> | | | | | |
| 1.2.1 የአበባ ልማት | ከ10-30 | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| | ከ30 በላይ | አይፈቀድም | አንድ | አንድ | አንድ |
| 1.2.2 በርበሬና ቅመማ -ቅመም ማልማት | ከ50-100 | አይፈቀድም | ሁለት | አንድ | ሶስት |
| | ከ100 በላይ | አይፈቀድም | ሁለት | አንድ | ሶስት |
| 1.3. <u>ቋሚ ተክሎች ልማት</u> | | | | | |
| 1.3.1 ቡና እና/ወይም ሻይ ቅጠል ማልማት | 200-300 | አንድ | ሶስት | አንድ | ሶስት |
| | ከ300 በላይ -1000 | አንድ | አራት | ሁለት | አራት |
| 1.3.2 የጎማ ዛፍ፣ ጃትሮፋ እና/ወይምፓልም ማልማት | ከ1000 በላይ-2000 | አንድ | አምስት | ሦስት | አምስት |
| | ከ2000 በላይ-3000 | አንድ | ስድስት | አራት | ስድስት |
| | ከ3000 በላይ-4000 | አንድ | ሰባት | አምስት | ሰባት |
| | ከ5000 በላይ | አንድ | ስምንት | ስድስት | ስምንት |
| 2. <u>የእንስሳት ሀብት ልማት</u> | | | | | |
| 2.1 የቤት እንስሳት እና/ወይም የዱር እንስሳት እርባታ እና ተዋጽኦ ልማት(ማደለብን ሳይጨምር) | ከ200-500 | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| | ከ500 በላይ | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| 2.2 የዶሮ እና/ወይም አዕዋፋት እርባታና ተዋጽኦ ልማት | 2,000-10,000 | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| | ከ10,000 በላይ - 50,000 | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | ሁለት |
| | ከ50,000 በላይ | አይፈቀድም | ሁለት | አይፈቀድም | ሶስት |

የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2

| ግብርና | የሚለማው መሬት ስፋት (በሄክታር) | በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | | በሌሎች አካባቢዎች | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ሞተር ብስክሌት | የጭነት መኪና | ሞተር ብስክሌት | የጭነት መኪና |
| 2.3. ንብ ማነብ/ማር ማምረት | 1,000ቀፎና በላይ | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| 2.4. የሐር ትል ማልማት | ከአንድ ሄክታር በላይ | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| 2.5. በሰው ሠራሽ ኩሬ የባህር እንስሳት/ዓሣ ማምረት | 1250ሜ.ኩ.እና በላይ | አይፈቀድም | አንድ | አይፈቀድም | አንድ |
| 3. የተጣመረ ግብርና (የእርሻና እንስሳት) ልማት | 200-300 | አንድ | ሶስት | አንድ | ሶስት |
| | ከ300 በላይ -1000 | አንድ | አራት | ሁለት | አራት |
| | ከ1000 በላይ-2000 | ሁለት | አምስት | ሦስት | አምስት |
| | ከ2000 በላይ-3000 | ሁለት | ስድስት | አራት | ስድስት |
| | ከ3000 በላይ-4000 | ሁለት | ሰባት | አምስት | ሰባት |
| | ከ5000 በላይ | ሶስት | ስምንት | ስድስት | ስምንት |
| 4. የደን ልማት እና ተዛማጅ ስራዎች | ከ100 ሄክታር በላይ | አንድ | አንድ | ሁለት | ሁለት |

## ሠንጠረዥ ሦስት

### ለኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት ሥራዎች ከቀረጥ ነጻ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች በኢንቨስትመንት ሥራ መስክና በተቋራጭነት ደረጃ

| ተራ ቁጥር | የኮንስትራክሽን ዘርፍ | ደረጃ አንድ | ደረጃ ሁለት | ደረጃ ሦስት | ደረጃ አራት | ደረጃ አምስት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት | | | | | |
| | የጭነት መኪና | ሁለት | ሁለት | ሁለት | ሁለት | - |
| | የውሀ መያዣ የተገጠመለት መኪና | አንድ | አንድ | - | - | - |
| | የውኃ መርጫ የተገጠመለት መኪና | አንድ | አንድ | - | - | - |
| | ግሬደር | ሶስት | ሁለት | አንድ | አንድ | - |
| | ኤክስካቫተር | ሶስት | ሁለት | አንድ | አንድ | □ |
| | ሎደር | ሶስት | ሁለት | አንድ | አንድ | □ |
| | ሮለር | ሶስት | ሁለት | አንድ | አንድ | □ |
| | ገልባጭ | አምስት | አራት | ሦስት | ሁለት | አንድ |
| 2 | የ ው ሃ ጉ ድ ጓ ድ ቁ ፋ ሮ | 1 ድሪሊንግ ሪግ፣ 1 ክሬን ትራክና 1 የጭነት መኪና፣ | | | | |
| 3 | የማዕድን፣ የነዳጅና የጂኦተርማል ቁፋሮ | 1 ድሪሊንግ ሪግ፣ 1 ክሬን ትራክ እና 1 የጭነት መኪና፣ | | | | |

## ሠንጠረዥ አራት

### የኮከብ ደረጃ ላላቸው የሆቴል (ሪዞርት ሆቴልን ጨምሮ)፣ የሞቴል፣ የሬስቶራንትና የሎጅ አገልግሎት ኢንቨስትመንቶች ከቀረጥ ነፃ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች በኮከብ ደረጃ

| ተ.ቁ. | የኮከብ ደረጃ | የተሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | 1 ወይም 2 | 2 ሚኒባስ እና 1 ሚዲባስ |
| 2 | 3 እና 4 | 3 ሚኒባስ እና 2 ሚዲባስ |
| 3 | 5 እና ከዚያ በላይ | 4 ሚኒባስ እና 3 ሚዲባስ |

## ሠንጠረዥ አምስት

### ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ ማስተላለፊያና ማሠራጫ ኢንቨስትመንቶች ከቀረጥ ነጻ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

| ተ.ቁ. | የማመንጨት አቅም | የተሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | እስከ 50 ሜጋ ዋት | 2 የጭነት መኪና |
| 2 | ከ50 ሜጋዋት በላይ - 150 ሜጋ ዋት | 3 የጭነት መኪና |
| 3 | ከ150ሜጋዋት በላይ | 4 የጭነት መኪና |

የገንዘብ
የሬከርድ
አስተዳደር
አገልግሎት
2

## ሠንጠረዥ ስድስት

## ስሎጂስቲክስ አገልግሎት ኢንቨስትመንት ሥራ መስክ ከቀረጥ ነጻ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

| የኢንቨስትመንት ሥራ መስክ | የተሽከርካሪ ዓይነት |
|---|---|
| **የሎጂስቲክስ አገልግሎት** | |
| 1. የቀዝቃዛ መጋዘን አገልግሎት | የጭነት መኪና |
| 2. የብትን ጭነት (ሳይሎ) መጋዘን አገልግሎት | የጭነት መኪና |
| 3. የደረቅ ወደብ አገልግሎት | የጭነት መኪና |

## ሠንጠረዥ ሰባት

## የትምህርትና ስልጠና፣ የጤና አገልግሎት፣ የአርኪቴክቸር እና ኢንጅነሪንግ ስራዎች የቴክኒክ ምርመራና ትንተና አገልግሎት፣ የገቢ እና ጅምላ ንግድ ኢንቨስትመንቶች ከቀረጥ ነፃ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች

| የኢንቨስትመንት ሥራ መስክ | የተሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት |
|---|---|
| 1. የትምህርት የስልጠና | |
| 1.1 የሁለተኛ ደረጃና ከፍተኛ ትምህርት | 2 ባስ 1 ሚዲባስ |
| 1.2 መዋዕለ ሕፃናት፣አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ | 2 ባስ 1 ሚዲባስ |
| 1.3 የቴክኒክና ሙያ ስልጠና(ስፖርትን ጨምሮ) | 2 ባስ1 ሚዲባስ |
| 2. የጤና አገልግሎት | |
| 2.1 ቴሪሸሪ የልዩ ሆስፒታል አገልግሎት | 3 ባስ 2 ሚኒባስ |
| 2.2 የሆስፒታል አገልግሎት | 2 ባስ 1 ሚኒባስ |
| 2.3 የምርመራ ማዕከል አገልግሎት | 2 ሚኒባስ |
| 2.4 የክሊኒክ አገልግሎት | 1 ሚኒባስ |
| 3. የአርኪቴክቸር እና ኢንጅነሪንግ ስራዎች የቴክኒክ ምርመራ እና ትንተና | |
| 3.1 የአርኪቴክቸር እና ኢንጅነሪንግ ስራዎች ተዛማጅ የቴክኒክ ማማከር አገልግሎት | 1 ሚኒባስ |
| 3.2 የቴክኒክ ምርመራ እና ትንተና | 1 ሚኒባስ |
| 3.3 የጂኦፊዚክስና የላቦራቶሪ አገልግሎት | 1 ሚኒባስ |
| 4. የገቢ ንግድ | |
| 4.1 ቡታጋዝ ወይም ቢትመን ማስመጣት | 1 የጭነት መኪና |
| 5. የጅምላ ንግድ | |
| 5.1 ነዳጅና የነዳጅ ምርቶችን ማቅረብ እና የራስን ምርት በጅምላ መሸጥ | |

የገንዘብ የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2

## ሠንጠረዥ ስምንት

## ለሠራተኛ ማጓጓዣ ከቀረጥ ነፃ የማፈቀዱ ተሽከርካሪዎች በቋሚ ሠራተኛ ብዛት

| የኢንቨስትመንት ሥራ መስክ | የተሽከርካሪ ዓይነትና ብዛት |
|---|---|
| ከ10 - 25 | 1 ሚኒባስ ወይም 1 ሚዲባስ |
| ከ26 - 50 | 2 ሚኒባስ ወይም 2 ሚዲባስ ወይም 1 አውቶቡስ |
| ከ50 - በላይ | 3 ሚኒባስ ወይም 3 ሚዲባስ ወይም 2 አውቶቡስ |

## ሠንጠረዥ ዘጠኝ

## ለማዕድን ስራዎች ከቀረጥ ነጻ የሚፈቀዱ ተሽከርካሪዎች (በማዕድን ሥራ መስክ)

| የፈቃድ አይነት | የማዕድን አይነት | የካፒታል መጠን (በብር) | የተሽከርካሪ አይነት | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ሞተር ብስክሌት | የጭነት መኪና |
| ምርት | ሜታል እና የከበሩ ማእድናት | ከ8 -15 ሚልዮን | አንድ | ሁለት |
| | | ከ15 ሚሊዮን- 30 ሚሊዮን | ሁለት | ሶስት |
| | | ከ30 ሚሊዮን በላይ | ሶስት | አራት |
| | የኢንዱስትሪና የኮንስትራክሽን | ከ3-15 ሚሊዮን | አንድ | ሁለት |
| | | ከ15-30 ሚሊዮን | ሶስት | ሶስት |
| | | ከ30 ሚሊዮን በላይ | አራት | አምስት |
| | የከበሩ ድንጋዮች | ከ3-15 ሚሊዮን | አንድ | አንድ |
| | | ከ15-30 በላይ | ሁለት | ሶስት |
| | | ከ30 ሚሊዮን በላይ | አራት | አምስት |
| | ጨው | ከ5-15 ሚሊዮን | አንድ | ሁለት |
| | | ከ15-30 ሚሊዮን | ሁለት | ሶስት |
| | | ከ30 ሚሊዮን በላይ | ሶስት | አምስት |
| | የጂኦተርማል ክምችት | ከ5-15 ሚሊዮን | አንድ | ሁለት |
| | | ከ15-30 ሚሊዮን | ሁለት | ሶስት |
| | | ከ30 ሚሊዮን በላይ | ሶስት | አምስት |
| ምርት (ለህብረት ስራ ማህበራት ብቻ) | ለሁሉም ማዕድናት | ከ1-5 ሚሊዮን | ሁለት | ሁለት |
| | | ከ 5 ሚሊዮን በላይ | ሶስት | ሶስት |

የገንዘብ የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2 ሚኒስቴር